# ተቃዋሚ ፖለቲከኞቻችንና የማይታረም ስሕተታቸው!

ይህ ጉዳይ ብዙ የሚገርመኝና ብዙ ሊያስጽፍ የሚችል ርእሰ ጉዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን "እከሌ የተባለው ፖለቲከኛ (እምነተ አሥተዳደራዊ)፣ እከሊት የተባለችው ፖለቲከኛ እያልኩ የእያንዳቸውን ሰብእና በመዘርዘር ነገርን ቢያበዙት ምን ጥቅም አለው?" ብየ አሰብኩና ዋነኛ ወላዊ ባሕርያቸውን በማንሣት ብተች በቂ ነው ብየ በማሰብ በጨረፍታ ላቀርብላቹህ መረጥኩ፡፡

ዛሬ ምሽት ሰኞ ጥቅምት 7, 2009 ዓ.ም. የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ (ነጋሪተ ወግ) የአማርኛውን ዝግጅት ክፍል እያዳመጥኩ ነበር፡፡ ከምሽቱ ዝግጅቶች አንዱ ቅዳሜ ጥቅምት 5, 2009 ዓ.ም. በፋና ሬዲዮ (ነጋሪተ ወግ) አዘጋጅነት ስለተደረገ ውይይት ከዶ/ር መረራ ጉዲና ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ነበር፡፡
ዶ/ር መረራ ከወያኔ አንጋፋ ባለሥልጣናት ውስጥ ከጠቅላይ ሚንስትሩና ከምክትላቸው በስተቀር ሁሉም እዚያ እንደነበሩ በመግለጥ የፖለቲካ ምኅዳሩ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ምክንያት ከድጡ ወደ ማጡ በገባበት በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነቱ ውይይት ፋይዳ የሌለው መሆኑን በውይይቱ ወቅት መናገራቸውን ከገለጹ በኋላ "ከውይይቱ በኋላ ከነኝሁ ባለሥልጣናት ጋራ ቁጭ ብለን እየተጫወትን አብረን ምሳ በላን!" ሲሉ ኩራት ኩራት እያላቸው ተናገሩ፡፡

ይሄኔ ነበር ሁኔታው እጅግ አስገረመኝና ብዙ ጊዜ ከእነኝሁ ፖለቲከኞቻችን ላይ የማስተውለውን አስቂኝ፣ አስገራሚ፣ አቁስል፣ አብሻቂና አዋራጅ  ተላላነትና ግብዝነት በተመለከተ ይህችን ጽሑፍ ለመጻፍ የታሰበኝ፡፡

ፖለቲከኞቻችን ብዙዎቹ ኧረ ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ (በድፍረት ሁሉም በአጠቃላይ! የማልለው ሦስት አራት የሚሆኑ ይሄ ክሴ የማይመለከታቸው አሉና ነው) እናም እነኝህ ሰዎች ምን ፍላጎት ስቦ ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር ) ውስጥ እንዳስገባቸው አላውቅም በሆነ ምክንያት ፖለቲካ ውስጥ ገቡ እንጅ ፖለቲካ ማለት ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንደሚሠራ፣ ፖለቲካ ምን ዓይነት ሰብእና እንደሚጠይቅ፣ ሸፍጥን ብልጠትን ጽናትን ቁርጠኝነትን ስልትን መካን መላበስ እንደሚጠይቅ (ሸፍጥ  ስል እንደ ወያኔ ሀገርና ሕዝብን ለማጥፊያ ሳይሆን ወያኔን የመሰለ ጠላት ወይም የጥፋት ኃይል ከውጭና ከውስጥ ሲያጋጥም ሴራውን ለማክሸፍና ሀገርና ሕዝብን ለመታደግ እንዲያስችል ነው) ፣ መቸና የት ምን መደረግ እንዳለበት ወዘተረፈውን ጨርሶ ምንም የማያውቁ ጮርቃዎች ናቸው፡፡

እጅግ የሚገርመኝ ይሄንን ያህል ዘመን ከወያኔ ጋር ሲያሳልፉ የትናንት ተሞክሯቸው ለዛሬ ያበረከተላቸው ትምህርትና ልምድ ጨርሶ ምንም የሌለና አሁንም ወያኔ በፈለገ ጊዜ እንደፈለገ እንደ እቃ መጠቀሚያ የሚያደርጋቸው መሆናቸው ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ ብዙ ጊዜ ልብ ብላቹህ እንደሆነ በቴሌቪዥን (በምርዓየ ኩነት) በመታየት፣ እንደዚህ ደግሞ ከዶ/ር መረራ እንደሰማቹህት በመብልና መጠጥ ግብዣ በመሳሰሉት ትንንሽ ነገሮች የሚደለሉ እንደ ልጅ በከረሜላ የሚታለሉ መሆናቸውን ሳይ እጅግ እጅግ ነው የሚገርመኝ የሚያበሳጨኝም፡፡
አሁን ማን ይሙትና እንዲህ ዓይነት ከንቱዎች ባይሆኑ ኖሮ "ሕዝባችን! ወገናችን! ምንትሳችን!" እያሉ የሚያንቆለጳጵሱት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕጋዊ የመቃወም መብቱን ስለተጠቀመ ብቻ ሴት ወንድ ሕፃን አዋቂ ሳይለይ በግፍ በየአደባባዩ እየተደፉ ባለበት በዚህ ሰዓት እንዴት ዓይነት ሞራል (ቅስም) ቢኖራቸውና እንዴትስ ቢዋጥላቸው ነው ከገዳዮቻቸው ጋራ በማዕድ ተሠይመው የሚበሉ የሚጠጡት??? እነዚህ ሰዎች ለግል ጥቅማቸውና ለሥልጣን ሲሉ ፖለቲካ ውስጥ የገቡ እንጅ እውነት ለዚህ የትም እየተደፋ ላለ መከረኛ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ እንዲያው ትንሽም እንኳ ሳይተናነቃቸው ደማቸውን ከሚያፈሱት አረመኔዎች ጋር እየተገባበዙ ይስተናገዱ ነበር??? እጅግ በጣም ያሳዝናል! ወያኔ እርማቸውን ነው እያስበላቸው ያለው፡፡

ሲጀመር እንኳን ቅራሪው ቀድሞውንም ዓይነታው አያምር እንደነበር እየታወቀ በሀገሪቱ በይፋ

ሕግና ሕገመንግሥታዊ መብቶች ተጥሰው ተሸረው በቦታቸው ፈላጭ ቆራጭ አረመኔያዊ ሕገ ወጥነት በአዋጅ በተተካበት ወቅት መጠቀሚያ ከመሆን በስተቀር የናንተ ውይይት ምን ይፈይድና ነው "ተወያየን!"ምንትስ የሚባለው???

ከወያኔ ጋር መቸና የት ያደረጋቹህት ውይይት ፋይዳ ኖሮት፣ መፍትሔ አምጥቶ ያውቃልና ነው "በዚህኛውም ውይይት አንዳች መፍትሔ እናገኛለን!" ብላቹህ ተስፋ በማድረግ ልትገኙ የቻላቹህት???
ከቶ መቸ ነው የምትበስሉት? መቸስ ነው ከልምድና ከተሞክሮ የምትማሩት? እስከመቸስ ነው በእናንተ ወራዳ ተግባር ሕዝብ እንዳሳፈራቹህ፣ እንዳዋረዳቹህ፣ እንዳማሸማቀቃቹ የምትኖሩት?

ዘለዓለም ከጮርቃነት የማትወጡ ፖለቲከኞቻችን ሆይ! እባካቹህ የሕዝባችንን ደም ደመ ከልብ አታድርጉብን፡፡ ሕዝባችን እያደረገ ባለው ትግል ደሙን የሚያፈስበት የከበረ ዓላማ አለው፡፡ ይህ ዓላማ እናንተን ለሥልጣን ማብቃት አይደለም፡፡ ይህ ዓለማ ሀገሩንና እራሱን ነጻ ማውጣትና የሥልጣን ባለቤት ማድረግ ነው፡፡ ያሳካዋልም!!

በዚህ መሀል ግን ለግል ጥቅማቹህ በመስበድበድ ይሄንን የከበረ ዓላማውን ያሚያደናቅፍ ወይም አቅጣጫ የሚያስት ወይም ወደ ኋላ የሚመልስ ተግባር ከወያኔ ጋር ተስማምታቹህ አንዳች ነገር ብትፈጽሙ ይህ ሕዝብ ከወያኔ ለይቶ እንደማያያቹህና ውድ ዋጋም ለመከፈል እንደምትገደዱ ጠንቅቃቹህ እንድታውቁት፡፡
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com